# የኢሲምባ የውይይት መድረክ
# ለፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ ራዲዮ
# ልዩ የዕርዳታ ዝግጅት ያደርጋል

## ቅዳሜ ኅዳር 27 ቀን 2012 (December 7, 2019)

## <u>የፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነት ድምፅ ራዲዮ ጣቢያን እንርዳ፡-</u>

የኢሲምባ የፓለቶክ ውይይት መድረክ ቅዳሜ ኅዳር 27 ቀን 2012 (እኤአ December 7, 2019) ከቀኑ 2:00 የዋሽንግተን ዲሲ ሰዓት አቆጣጠር ጀምሮ የገንዘብ እርዳታ ለማሰባሰብ በምናደርገው ዝግጅት ላይ በውጭ ያላችሁ አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን እንድትገኙልን በማክበር እንጋብዛለን።

የፍኖተ ራዲዮ ጣቢያ ለኢትዮጵያውያን፣ በኢትዮጵያውያን፣ ስለኢትዮጵያውያን የተቋቋመና፤ ከተመሠረተበትም ጊዜ አንስቶ በሀገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን እርዳታ ብቻ ፕሮግራሙን የቀጠለ ዕውነተኛ ኢትዮጵያዊ አማራጭ ራዲዮ ስለሆነ የሀገር ወዳዶችን እርዳታ ይሻልና ሁላችንም እንረባረብ። የፍኖተ ራዲዮ አገር ውስጥ ላሉ አድማጮች በሳተላይ የሚተላለፍ ሲሆን በውጭ ላሉ አድማጮች በኢንተርኔት፤ በማህበራዊ ሚዲያ፤ በዩቲዩብና በስልክ አማካይነት አገልግሎቱን በማዳረስ ላይ ይገኛል፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ አንዳንድ ፕሮግራሞቹን በምስል በኢንተርኔትና በሶሻል ሚዲያ ማስተላለፍ የጀመረ ሲሆን የገንዘብ አቅም ከፈቀደ ይህንኑ ወደ አገር ቤት በቴለቪዥን አማካይነት ለማሰራጨት ጥረት እያደረገ መሆኑም ይታወቃል፡፡

በተለይ ጠባቦችና ከፋፋዮች በሚያካሂዱት ውሥብስብ ሴራ አገራችን ከበድ ያለ የፖለቲካ ቀውስ በወደቀችበትና ህልውናዋ ላይ ከፍተኛ አደጋ በተጋረጠበት በአሁኑ ወቅት ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ የአገራችንን ሁለንተናዊ ሁኔታዎች የሚገመግሙ፤ አደጋዎችን አስቀድሞ በማየት አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን አገራቸውንና ለማዳንና ሕዝባቸውን ለመታደግ ማድረግ የሚገባቸውን ተግባርና አቅጣጫ በመጠቆም የሚያስተላልፋቸው ትምህርታዊ ዝግጅቶች ከፍተኛ ግምት የሚሰጣቸው ስለሆነ እርዳታችንን በመለገስ የራዲዮ ፕሮግራሙን እናጠናክር።

በዚህ ዕለት የኢሕአፓ አመራር አባላት በመድረኩ ተገኝተው ስለ አገራችን ወቅታዊ ሁኔታ ገለጻ የሚሰጡ ሲሆን የራዲዮ ጣቢያው የዝግጅት ክፍል አባላትም የራዲዮ ጣቢያው ስላለበት ሁኔታና እያደረገ ስላለው አስተዋጾ ማብራሪያ ይሰጣሉ። በዕለቱ በመድረካችን በመገኘት ስለአገራችንም ሁኔታም ሆነ ስለ ራዲዮ ጣቢያው ያላችሁን ጥያቄ በማቅረብና ጠቃሚ አስተያየቶችን በመስጠት ተሳታፊ እንድትሆኑ እየጋበዝን ለራዲዮ ጣቢያውም እርዳታችሁን እንድትለግሱ የአክብሮት ጥሪያችንን እናስተላልፋለን።

የአሲምባ የፓልቶክ የውይይት መድረክ በየሳምንቱ ቅዳሜ በዋሺንግተን ዲሲ ሰዓት አቆጣጠር ከቀኑ 2 ሰዓት ጀምሮ የሚከፈትና እነሆ ለለፉት 13 ዓመታት የሀገራችንን ፖለቲካ ሁኔታ በሚመለከት የተለያዩ በሳል ሀሳቦች የሚንሸረሸሩበት ዴሞክራሲያዊ የውይይት መድረክ ነው።

የአሲምባ ውይይት መድረክ